ምድብ አምስት (ከ10ኛ -12ኛ ክፍል)

31ኛ ሳምንት

ዕርገት

ዓላማ

❖ ስለክርስቶስ ዕርገትና ከማረጉ በፊት ያስተማረውን ትምህርት መማር

የሚጠና ጥቅስ

❖ ***" እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ"*** የሐዋ./ሥ.1÷8

ምንባባት

❖ ማር.16÷19-20 ሉቃ.24÷50 የሐ./ሥ.1÷6-11

የክለሳ ጥያቄዎች

1.ክርስቶስ በባሕር ዳርቻ ሲገለጥላቸው ደቀመዛሙርቱ ምን ያደርጉ ነበር?

2.ጌታ ጴጥሮስን ምን? ጠየቀው ስንቴ?

3.የጴጥሮስ መልስ ምን ነበር? ጌታስ ምን አዘዛቸው?

ምንባባት

❖ ማር16÷19-20 ሉቃ.24÷50-53 የሐዋ./ሥ 1÷13-11

መግቢያ

❖ ኢየሱስ ክርስቶስ ለ33 ዓመታት በምድር ኖሯል።በ30 ዓመቱ ተጠመቀ ለ3ዓመታት አስተማረ ፣ስለኃጢያታችን በመስቀል ላይ ቤዛ ሆነልን።በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሳ ለደቀመዛሙርቱም ተገለጠላቸው።
❖ ዛሬም ከማረጉ በፊት ከተነሳ በኋላ ስላስተማራቸው ትምህርቶች እና ደቀመዛሙርቱን ያዘዛቸውን ትዕዛዝ እንማራለን።

ትምህርቱ

❖ ጌታችን ከተነሣ በኋላ ባሉት 40ቀናት በተለያዩ ጊዜ ለደቀመዛሙርቱ ተገልጾ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ያስተምራቸው ነበር።
❖ ስለክርስቶስ የተነገረውን የቅዱሳት መጻሕፍት ትንቢት ከዚያ በፊት አላስተዋሉም ነበር።
❖ ጌታችንም ስለ እርሱ የተጻፉትን ተረጎመላቸው አዕምሮአቸውንም ከፈተላቸው መጻሕፍትንም አስተዋሉ።እምነታቸውን አጸናላቸው። ስለትንሳኤው የነበራቸውን ጥርጣሬም አጸዳላቸው።
❖ የሚከተሉትን ትዕዛዛት እና ኃላፊነቶችም ሰጣቸው

1. ***ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ*** ። ማር 16÷15
2. ***ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ*** የሐዋ./ሥ 1÷5
3. ***እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁቸው... አስተምሯቸው*** ማቴ.28÷19-20
4. ***" እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ"*** የሐዋ./ሥ 1÷8

❖ በወንጌል ለመስበክ እና በስሙ ለማጥመቅ ወደ ዓለም ሲወጡ፣ እንደሚገረፉ ወደ ነገሥታት የፍርድ አደባባይም እንደሚያወጧቸው ነገሯቸዋል።እስከመጨረሻም የጸና ግን ይድናል።
❖ እስከዓለም ፍጻሜ ከእነርሱ ጋር እንደሚሆንና መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ኃይልን እንደሚያገኙም ቃል ገብቶላቸዋል።

- በተነሳ በ40 ኛው ቀን ደቀመዛሙርቱ ወደ ደብረዘይት ወሰዳቸውና ባረካቸው፡፡ተሰብስበው ትምህርቱን እየሰሙም *ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ አለ፡፡ወደ ሰማይም ዐረገ ደመናም ከዐይናቸው ሰወረው፡፡*
- ደቀመዛሙርቱ ክርስቶስ ወደ ዐረገበት ቀና ብለው እየተመለከቱ ሳለ ሁለት መላእክት ነጫጭ ልብስ ለብሰው በአጠገባቸው ቆመው *"ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይሄ ከናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሏቸው፡፡"*
- ደቀመዛሙርቱም ጌታ ካረገበት ከደብረዘይት እግዚአብሔርን እያከበሩ ተመለሱ፡፡
- እንደታዘዙት መንፈስ ቅዱስን እስኪቀበሉም በእየሩሳሌም ቆዩ ፡፡

<u>ማጠቃለያ</u>

- ጌታ ከተነሳ በኂላ በ40ውን ቀናት እያስተማረ እና ሐዋርያትን እያዘዘ ከቆየ የሚያገኛቸውን መከራ ነገራቸው የሚጸና ዘላለማዊ ህይወት እንደሚያገኝ ቃል ገባላቸው፡፡ በደብረ ዘይት ሰብስቦ አስተምሮ ባርኳቸው ዐረገ ፡፡
- እንደ ክርስቲያን ምስክሮች ልንሆን ተጠርተናል፡፡ ምስክርነትም መናገር ብቻ ሳይሆን ትዕዛዛቱን መጠበቅ ነው፡፡ ***ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ*** ማቴ.28÷20

<u>ጥያቄዎች</u>

(1) ጌታችን ከተነሳ በኂላ በምድር ላይ ስንት ቀን ቆየ

______________________________

(2) ደቀ መዛሙርቱ ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?

______________________________

(3) በማን ስም እንዲያጠምቁስ አዘዛቸው?

______________________________

(4) ክርስቶስ ሲያርግ ደቀመዛሙርቱን የት ሰበሰባቸው?

______________________________

(5) መላእክት በክርስቶስ ዕርገት ተገልጠው ለደቀመዛሙርቱ የነገሯቸው ምንድነው?

______________________________

(6) ጌታ ስለ እኛ ከመሰቀሉ በፊት ለደቀመዛሙርቱ በደብረዘይት ያስተማራቸው ምን ነበር?

______________________________

(7) ደቀመዛሙርቱ ለማስተማር ሲወጡ ምን እንደሚያገጥማቸው ነው ጌታ ቀድሞ ያስጠነቀቃቸው?

______________________________

ይቆየን….